ኮንክሪት ወይም አስፋልትን በአስተላላፊ ንጣፎች ወይም ዕፅዋት ለመተካት ተመላሽ ማግኘት ይፈልጋሉ?

ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

የንብረት ባለቤቶች በዲሲ ውስጥ ባሉ መኖሪያ ህንጻዎች፣ የንግድ ህንጻዎች ወይም ኢላማ በተደረገባቸው አካባቢዎች ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ ቦታዎች ላይ (በዚህ ካርታ ላይ ያሉ ሰማያዊ ምልክቶች) ኮንክሪት፣ አስፋልት፣ ወይም ሽክላን በአስተላላፊ ንጣፎች ወይም ዕፅዋት ሲተኩ ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ። አስተላላፊ ገጽታዎች የተበከለ ውሃ ወደ ወንዞቻችን እንዳይገባ ለመቀነስ የዝናብ ውሃን ይዞ በጊዜያዊነት ያጠራቅማሉ። እኛ —የዲሲ መንግስት—በእጽዋት ለሚተኩት ገጽ **$5 በስኩዌር ጫማ**የሚሆን እንዲሁም በአስተላላፊ ገጾች የተተካበት **$10 በስኩዌር ጫማ** የአንድ ጊዜ ተመላሽ ያቀርባል። እስከ **$4,000** የሚሆን እና ከፕሮጀክትዎ ወጪ የማይበልጥ ገንዘብ ሊቀበሉ ይችላሉ።

ይህ ፕሮግራም RiverSmart ተመላሾች ሲባል የቀረበውም በሃይልና አካባቢ ዲፓርትመንት ከ Alliance for the Chesapeake Bay (ወይም በአጭሩ Alliance ይባላል) ከሚባል ለትርፍ ከማይሰራ ድርጅት ጋር በመተባበር ነው።

ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

እነዚህ መግለጫዎች በሙሉ እውነት ከሆኑ፣ እርስዎ ብቁ ነዎት ማለት ነው:

- በዲሲ ውስጥ የመኖሪያ ህንጻ፣ የንግድ ህንጻ፣ የአምልኮ ቤት ወይም የማህበረሰብ ስፍራ ካለዎት።
- ንብረትዎ በዲሲ መዘጋጃ ቤት የፍሳሽ ማስወገጃ ሲስተም ውስጥ ከሆነ። በዚህ ካርታ ላይ አድራሻዎን ይፈልጉ እና በሰማያዊ የሆነው ህንጻ ላይ ከሆነ፣ ንብረትዎ ለፕሮግራሙ ብቁ ነው።
- ህንጻዎ በአካባቢው ያለ የዝናብ ውሃ መቆጣጠሪያ መስፈርቶችን ማሟላት ካስፈለገው፣ ፕሮጀክትዎ እርስዎ እንዲያደርጉ ከሚያስፈልግዎ በላይ ይሄዳል። እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ስለብቁነትዎ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ Carly Starobin (cstarobin@allianceforthebay.org) ያነጋግሯት።

የሚያመለክቱበት ንብረት ዲሲ ውስጥ እስከሆነ ድረስ ለማመልከት ዲሲ ውስጥ መኖር አይጠበቅብዎትም።

ያመልክቱ።

1. ዕፅዋት ወይም አስተላላፊ ንጣፎችን ማድረግ እንደሚፈልጉ ይለዩ። አካባቢው ለምን አገልግሎት እንደሚውልና ምን ያህል ትልቅ እንደሚሆን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብዎታል። ለንብረትዎ ምርጥ ምርጫ ጥያቄዎች ካለዎት፣ በአካባቢው የእኛ ትርፋማ ያለሆነ አጋር የሆነውን the Alliance for the Chesapeake Bay በ Carly Starobin (cstarobin@allianceforthebay.org) በኩል እርዳታ ለማግኘት ያነጋግሯት!

2. በእኛ አስተላላፊ ገጽታዎች መመሪያ ላይ የፎቶ ጠቃሚ ምክሮችን በመከተል በማመልከቻዎ ውስጥ ለማካተት፣ መጀመሪያ የነበረውን "የቀድሞ" ገጽታ ፎቶዎች ያንሱ።
3. የስራ ተቋራጭ ወይም የመሬት ገጽታ ባለሙያ ይምረጡ። አስተላላፊ ንጣፎችን የሚዘረጉ ከሆነ፣ ተመሳሳይ ፕሮጀክት እና "PICP የምስክር ወረቀት" የሚባል ልዩ ስልጠና ያጠናቀቀ ማንኛውንም ስራ ተቋራጭ መምረጥ ይችላሉ። ከተመላሽ ፕሮግራም ጋር የሚተዋወቁ የስራ ተቋራጭ ዝርዝሮችን አቅርበናል። ዕፅዋትን ከተከሉ፣ ከማንኛውም የመሬት ገጽታ ባለሙያ ጋር ወይም ራስዎ ብቻ ፕሮጀክቱን ሊሰሩት ይችላሉ።
4. የውሃ ፍሳሾች ከአፈሩ በምን ያህል ፍጥነት እንደሚፈስሱ ለማየት የመረጡትን ስፍራ ይመርምሩ። ይህ የ percolation ምርመራ (ወይም በአጭሩ perc ምርመራ) ይባላል። የ perc ምርመራ ወርክሺትን በማመልከቻዎ ውስጥ ያጠናቅቁ። ከስራ ተቋራጭ ጋር የሚሰሩ ከሆነ፣ በዚህ ደረጃ ላይ ሊረዳዎት ይችላል።
5. የንድፍ ስኬች እና በእያንዳንዱ ንጥል ያለ በጀት ያዘጋጁ። በእኛ አስተላላፊ ገጽታዎች መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ንድፍዎ ማሟላት አለበት። ለበጀትዎ በማመልከቻው ጥቅል ውስጥ ያለውን የናሙና ንጥል የመክፈያ ደረሰኝ ወርክሺት መጠቀም ይችላሉ። ከስራ ተቋራጭ ጋር የሚሰሩ ከሆነ፣ በዚህ ደረጃ ላይ ሊረዱዎት ይገባል። የንድፍ እና የክፍያ ደረሰኝ ክፍሎችን ከማጠናቀቅ ይልቅ፣ ፕሮፖዛላቸውን ማመልከቻው ላይ ማያያዝ ይችላሉ።
6. የማመልከቻውን ቅጽ እና የጥገና ስምምነቱን ያጠናቅቁ። RiverSmart Rewards በሚባለው በእርስዎ DC Water ክፍያዎ ላይ ለቅናሽ ለማመልከት፣ ለእርስዎ በማመልከቻው ጥቅል ውስጥም እንዲሁም ቅጽ አካትተናል። ከ1,200 በላይ ስኩዌር ጫማ አስተላላፊ ንጣፎችን የሚዘረጉ ከሆነ፣ ተጨማሪ ወርክሺት እንዲሁ መሙላት ይጠበቅብዎታል።
7. የተሞላውን ማመልከቻ፣ የጥገና ስምምነት፣ perc የምርመራ ወርክሺት፣ ንጥል የክፍያ ደረሰኝ እና ከመሰራቱ በፊት ያሉ ፎቶዎችን ያስገቡ። ወደ Carly Starobin በ the Alliance (cstarobin@allianceforthebay.org) በኩል ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ ወይም ወደሚከተለው በፖስታ ይላኩ:

   Carly Starobin
   Alliance for the Chesapeake Bay
   729 8th Street SE, Suite 200
   Washington, DC 20003

የዝናብ አትክልት ስፍራዎትን ከመስራትዎ በፊት፣ እኛ ጋር ባለው አስተላላፊ ገጽታዎች መመሪያ መስፈርቶች በሙሉ ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ አመልክተው ተቀባይነት ለማግኘት መጠበቅ አለብዎት። ፕሮጀክትዎ ከተሰራ እስከ አንድ አመት ውስጥ ማመልከቻዎን ካስገቡ፣ ማመልከቻዎን ከግምት ውስጥ እናስገባዋለን። ይሁን እንጂ በእኛ ላይ ባለው አስተላላፊ ገጽታዎች መመሪያ መስፈርቶች በሙሉ ካላሟላ፣ ለተመላሽ ብቁ አይደለም ማለት ነው።

የበለጠ መረጃ ይሰብስቡ።

ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. ከ 1-3 ሳምንታት ውስጥ፣ Alliance for the Chesapeake Bay (ወይም በአጭሩ the Alliance) ማመልከቻዎን ይገመግማል። የአስተላላፊ ገጽታውን ለመስራት ያቀዱበትን ቦታ መርሃ ግብር ይዞ ለመመርመር ኢሜይል ያደርጉልዎታል ወይም ይደውሉልዎታል። በRiverSmart Homes ፕሮግራም በኩል ምርመራ ቀድሞ ካስደረጉ፣ ሌላ ምርመራ አያስፈልግዎትም።
2. ማመልከቻው በ the Alliance ተቀባይነት ካገኘ በኋላ፣ እራስዎ ወይም ስራ ተቋራጩ የአስተላላፊ ገጽታውን ይስሩ። ከእርስዎ የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽ ጋር ለማካተት፣ እንደ አማራጭ የቀረበ ነው ነገር ግን የሚችሉ ከሆነ፣ የስራውን የሂደት ፎቶዎች ያንሱ (ደረጃ #5 ይመልከቱ)። ለደረጃ #5 ማንኛውንም የክፍያ ደረሰኞችን መመዝገብዎን ይቀጥሉ።
3. በእኛ የአስተላላፊ ገጽታዎች መመሪያ ላይ ያሉትን የአስተላላፊ ሁሉንም ገጾች መስፈርት እንዳሟሉ ለማሳየት፣ "በኋላ" የተሰራውን የአስተላላፊ ገጽታ ፎቶዎች ያንሱ። ከፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽዎ ጋር ለማካተት እነዚህን ይያዙ (ደረጃ #5 ይመልከቱ)።
4. የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽን ከመጨረሻው የንድፍ እና የአስተላላፊ ገጽታዎች ወጪ መረጃ ጋር ያጠናቅቁ።
5. የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽዎን፣ ሁሉም የተከፈሉ ደረሰኞች እና ከስራው በኋላ ያሉትን ፎቶዎች ለ Carly Starobin በ cstarobin@allianceforthebay.org ላይ ያስገቡ።
6. ከ 1-3 ሳምንታት ውስጥ፣ የአስተላላፊ ገጽታ የሰሩበትን ስፍራ የመመርመር መርሃ ግብር ለማስያዝ the Alliance ኢሜይል ያደርግልዎታል ወይም ይደውልልዎታል።
7. ፕሮጀክትዎን the Alliance ከመረመረና ካጸደቀ በኋላ ባሉት ከ 2-6 ሳምንታት ውስጥ፣ በማመልከቻዎ ላይ ባለው አድራሻ ለተመላሽዎ በፓስታ ቼክ ይልክልዎታል።
8. የእኛን የጥገና መመሪያ በመከተል ተክሎችን ማጠጣት፣ አረም ማረም እንዲሁም መጥረግን በማካተት የአስተላላፊ ገጹን ይጠብቁታል እንዲሁም ይንከባከቡታል። ምክር ከፈለጉ፣ ለ Carly Starobin በ cstarobin@allianceforthebay.org ላይ ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።
9. ሁሉም ነገር በትክክል እንደተጠበቀ ለማረጋገጥ፣ DC Government ወይም the Alliance በዘፈቀደ ቤትዎን ሊመርጡት ይችላሉ። ፕሮጀክትዎ ከተመረጠ፣ የምርመራውን መርሃ ግብር ለማስያዝ ኢሜይል እናደርግልዎታለን ወይም እንደውልልዎታለን።

ማመልከቻው የእኛን መስፈርቶች ካላሟላ፣ ማመልከቻዎ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ ምን አይነት ለውጦች ማድረግ እንደሚችሉ እናሳውቅዎታለን። ማመልከቻዎን እንደገና እንድንገመግምልዎ፣ የተከለሰ የንድፍ ስኬች፣ የንጥል ክፍያ ደረሰኝ፣ perc ምርመራ ወርክሺት እና/ወይም ከስራው በፊት ያሉ ፎቶዎችን መላክ ሊያስፈልግዎት ይችላል።

ሁሉም ብቁ አመልካቾች ተመላሹን ያገኛሉ?

አዎ። በእኛ አስተላላፊ ገጽታዎች መመሪያ ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የእርስዎ ፕሮጀክት ካሟላ፣ ተመላሽ ያገኛሉ። ካመለከቱ በኋላ የፕሮጀክትዎን ዲዛይን ላይ ለውጥ ካደረጉ፣ ተመላሹን አሁንም

ማግኘት የሚችሉ እንደሆነ ለማየት Carly Starobin (cstarobin@allianceforthebay.org) ያግኟት።

ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

በፕሮጀክትዎ ዕፅዋትን የሚጠቀሙ ከሆነ ቢያንስ 200 ስኩዌር ጫማ ወይም አስተላላፊ ንጣፎችን የሚጠቀሙ ከሆነ ደግሞ 100 ስኩዌር ጫማ መሆን አለበት።

ለፕሮጀክትዎ ፈቃዶች ሊያስፈልግዎ ይችላል። ለፈቃድ መስፈርቶችና ፈቃድ ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት፣ በሸማች እና ቁጥጥር ጉዳዮች መምሪያ የቤት ባለቤቶች ማዕከልን ይጎብኙ።

ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?
መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች ቦታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎ Carly Starobin በ Alliance for the Chesapeake Bay ላይ በስልክ ቁጥር (202) 903-6533 ያነጋግሯት። ወይም ለ Carly በ cstarobin@allianceforthebay.orgላይ በርዕሰ መስመር “Permeable Surface Rebate Question” ብለው ኢሜይል መላክ ይችላሉ።

ስለፕሮግራሙ በዲሲ መንግስት ውስጥ ያለን አንድ ሰው ለማነጋገር ከፈለጉ፣ እባክዎን የእኛን RiverSmart Homes ቡድንን በ (202) 535-2252 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ፣ ከ 9 am እስከ 5 pm ባለው ሰዓት ውስጥ ያግኙ። ወይም ወደ እኛ በriversmarthomes@dc.gov በርዕሰ መስመር “Permeable Surface Rebate Question” ብለው ኢሜይል መላክ ይችላሉ።

በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?
ቤትዎን ለአካባቢ ተስማሚ የሚያደርጉ እርስዎን ሊረዱ የሚችሉ ሌሎች መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች
ተመላሼ የሚሰላው እንዴት ነው?

ተመላሽ የሚሰላው በጸዳው አካባቢ ስፋት ላይ ተመስርቶ ነው። **$5 በስኩዌር ጫማ** የሚሆን እንዲሁም በአስተላላፊ ገጾች ለሚተኩት **$10 በስኩዌር ጫማ** ያገኛሉ። እስከ **$4,000** የሚሆን ወይም የፕሮጀክትዎን ወጪ ይቀበላሉ። ለምሳሌ፣ 200 ስኩዌር ጫማ የሸክላ በረንዳን በአስተላላፊ ንጣፎች ከተኩ፣ $2,000 ተመላሽ ያገኛሉ። በአካባቢው ባሉ ተክሎች ወይም ሳር በመሰሉ እጽዋት ከተኩት፣ $1,000 ተመላሽ ያገኛሉ።

የጥላ ዛፍ እና የዝናብ አትክልት ስፍራዎችን የመሳሰሉ ሌሎች የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ተመላሽ ለማድረግ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

በራስዎ ወይም እርስዎ በመረጡት ገንቢ ባለሙያ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶችን ሲገነቡ፣ ከእኛ - የዲሲ መንግስት ተመላሽ መቀበል ይችላሉ። የብቁነት መስፈርት፣ የማመልከቻ ሂደት፣ እንዲሁም የተመላሽ መጠን በፕሮጀክቱ አይነት ላይ በመመስረት ይለያያል። ከመዘርጋትዎ በፊት መተግበር ሊያስፈልግዎ ይችላል። ተመላሽ ስለምንሰጥባቸው የሚከተሉት ፕሮጀክቶች የበለጠ መማር ይችላሉ፡

- የዝናብ ውሃን ለመያዝ የሚያስችሉ ተክሎችን እድገት ለመርዳት የሚሆኑ **አረንጓዴ ጣሪያዎች**
- **የዝናብ አትክልት ስፍራዎች** የተበከሉ የዝናብ ውሃ ፍሰትን ለመያዝ የሚረዱ
- በኋላ ላይ የአትክልት ቦታዎን ለማጠጣት ወይም መኪናዎን ለማጠብ የሚሆን የዝናብ ውሃ የሚያጠራቅምና የሚይዙ **የዝናብ በርሜሎች**
- **በአፈሩ ላይ የዝናብ** ውሃ ማቆየትን ለመርዳት የጥላ ዛፎች

አስተላላፊ ገጽታዎችን በማድረጌ ሌላ የገንዘብ እርዳታ ላገኝ እችላለሁ?

አዎ! ለዚህ ፕሮግራም ሲያመለክቱ፣ በ DC Water ክፍያዎ ላይ RiverSmart Rewards ለሚባለው ቅናሽ ማመልከት እንዲችሉ እንረዳዎታለን። ይህ ቅናሽ እንደ አስተላላፊ ንጣፎች ያሉ የበቁ አረንጓዴ ፕሮጀክቶችን በመጠቀም የውሃ ፍሰትን በንብረታቸው ላይ እንዳይሆን ለሚከላከሉ የንብረት ባለቤቶች ነው።

እነዚህ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች የዲሲ ከተማን እንዴት ብለው ሊረዱት ይችላሉ?

እንደ ዝናብ በርሜሎች፣ የዝናብ አትክልት ቦታዎች እንዲሁም የጥላ ዛፎችን ያሉ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ወደ ንብረትዎ እና ወንዞችዎ የሚፈስሰውን የተበከለ የዝናብ ውሃ መጠን ለመቀነስ ይረዳል። ይህ የ Anacostia ወንዝን፣ Potomac ወንዝን እና Rock Creek ከጎጂ ብክለት እንድንጠብቃቸው ይረዳናል።

ተቀባይነት ሳላገኝ ብቀር ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?

አዎ። በሁኔታዎ ላይ ያለው ለውጥ ብቁ ያደርገኛል ብለው ካመኑ፣ እንደገና ለተመላሽ ማመልከት ይችላሉ።

ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።